# ከመተንፈስም በላይ... የሚቻልባት ሀገር

አፈጩሊ (ከአሜሪካ ግቢ)

የስደት መልኮች ብዙ ዓይነት ናቸው። በተለይ ግን ጦርነት ለስደት መነሻነት በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው፤ ከሥራ አጥነት ጋር ተያይዞ ስደትን አማራጭ የሚያደርጉም አያሌዎች ናቸው። የችግሩ መንስኤ ፖለቲካዊ ሆኖ የሚታይበትም አጋጣሚ ይኖራል።

በዓለማችን የየትኛው ሀገር ሕዝብ በየትኛው ምክንያት እየተሰደደ እንደሆነ ማወቅ የእዚህ ጽሑፍ ትኩረት አይደለም፤ ስደተኞችን በመቀበል አውሮፓ ቀዳሚዋ አህጉር መሆኗን መንገርም ላይ አያተኩርም።

የእነማን ሀገር ስደተኞች በፖለቲካና መሰል ጉዳዮች እንደተሰደዱ፣ በእዚህም እንደተሸለሙ ለማወቅ የመረጃ ቋት ውስጥ ገብቶ መመርመር አያሻም። የመረጃ ቋቱ ባለቤቶች እነማን እንደሆኑ ለሚያውቅ በቁጥር መቶ፣ በመልዕክትና በአስተሳሰብ አንድ ተደርጎ የተከማቸን መረጃ ሲያማርጥ ቢውል የሚያገኘው መልስና መልዕክት አንድ ነው። በሌላ አነጋገር መቶ ጠጣ አሰልፎ ቆንጆዋን ምረጥ እንደማለት ነው።

በእዚህ አማራጭ አልባ ምርጫ ውስጥ የመግባትና የመካድ ውሸት ብቻም አይደለም የመረጃ ጥማትን የሚዘጋው ይልቅ በቋቱ ውስጥ መረጃ ቀማሪዎቹ የፖለቲካና የጥላቻ አተያያቸውን ሆነ ብለው ለማደናገር በማሰብ እንድንጋተው የሚጠቀሙበት ስልት ነው።

እናም ይህን አማራጭ አልባ «መቶ» አንድ ዓይነት መረጃ ነፃነት አልለውም። መቶውም በተለያየ ስልትና የታቀደ አጠቃቀም አንድ ሃሳብ እንዲያስተ ላልፍ ተደርጎ ከተቀመጠ አማራጭም አይሆንም። እንዲህም ብዬ ግን ፍፁም አልጨፍንም። በእዚህ መካከል ሌሎች ቋቶችን ለመበርበርና ለመፈተሽ እሞክራለሁ፤ ምክንያታዊ ሆኜ በማወቅ ለመመርመርም እሞክራለሁ። ከየትኛው ሀገር ምን ያህል ሰው እንደተሰደደ ለማወቅ ብቻ ሳይሆን የትኛው ዓይነት ስደት ምክንያት ሆኖ እንደሚቀርብም አጤናለሁ።

ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገሮች በዲቪ ሎተሪም፣ በጀልባም፣ ድንበር አቋርጦም፣ ለሥራና ለትምህርት ወጥቶ በእዚያው የሚቀር ተሰዳጅ እንዳለ እናውቃለን። ስደቱ ከተሳካ በኋላ ደግሞ የመኖሪያ ፍቃድና ሥራ ለማግኘት የመሰደዱ ምክንያት ፖለቲካዊ ሆኖ እንደሚቀርብም ግልጽ ነው። ለምሳሌ ያህል እዚህ በሀገር ውስጥ ፖለቲካውን ሲዘውሩት የነበሩ ሳይቀሩ ወጣ ሲሉ የመሰደዳቸውን ምክንያት ጫናና ወከባ መሆኑን ሲገልፁ መስማት አዲስ አይደለም። የፖለቲካ ወሬ ሰምቶም አይቶም የማያዋቅ ጉብል በአውሮፓ አገሮች መጠጊያ ለማግኘት በየፍርድ ቤቶቹ ጠበቃ አቁሞ የሚከራከረው በፖለቲካዊ አቋሙ ምክንያት መሰደዱን ምክንያት በማድረግ ነው።

ለመስራት እስከሆነ ድረስ መዋሸቱ ምንም አይደል በሚል ዝም ማለትን የመረጠ የሚመስለው መንግሥት በሰው ሀገር የተሻለ ሥራና ጥቅም ለማግኘት ምክንያት የሚደረድሩ ዜጎቹን ይቀየማል ተብሎ አይታሰብም። እነዚያው ዜጎች ነገ ሀገራቸውን የሚለውጥ ካፒታል ፈጥረው ወደ ሀገራቸው በመምጣት እንደሚያለሙና ለወገናቸው ቤዛ እንደሚሆኑም ያውቃል ተብሎ ይገመታል። በጋዜጠኝነት ሰበብ የፖለቲካ ጫናና ወከባ እንግልትም ደረሰብን ብለው ቁጥር ለማስመዝገብ የሚታትሩ ወገኖች ጉዳይ ግን አስተዛዛቢ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ጋዜጠኝነት ሙያዊ ኃላፊነትን ብቻ ሳይሆን መስዋዕትነት መክፈልን የሚጠይቅ የተከበረ ሙያ ነው። በጫና ሳቢያ ወደ ውጭ ተሰድጃለሁ የሚል ጋዜጠኛ ነኝ ባይ ግለሰብ አዲስ ጉዳይ መጽሔት እንደጠቀሰችው በራሱ የፖለቲካ አተያይ ለመጓዝ የመረጠ ግለሰብ እንጂ ጋዜጠኛ አይደለም። ጋዜጠኝነት ህዝብና ሀገር ውስጥም ነው።

የአዲስ ጉዳይ ቅፅ 7 ቁጥር 161 የሚያዚያ 2005 መጽሔት የጽሑፌ መነሻ ነው። የመጽሔቷ አቋም የሆነው ርዕሰ አንቀፅ እና «መንግሥት ለእዚህስ ምን መልስ አለው?» በሚል ያቀረበው ጉዳይ ላይም አተኩራለሁ። በቅድሚያ ግን አዲስ ጉዳይ «የጋዜጠኞች ስደትና እስር እንዲቆም» የሚል ርዕስ ባለው አቋሟ ያሰፈረችውን ሃሳብ በሁለት ፈርጅ ከፍሎ መመልከት ይገባል።

## ጉዳይ አንድ

ጋዜጠኞች ፖለቲከኞች ስላለመሆናቸው፣ መንግሥት በጋዜጠኞችና በፖለቲከኞች መካከል ስላለው

ልዩነት እንደማያውቅ ወይም አውቆ እንደማያውቅ፣ ጋዜጠኞችን የፖለቲካ ጥቃት ኢላማ የማድረግ ፍላጎት እንዳለው፣ ጋዜጠኛ እውነትን የማሳወቅ እንጂ ስልጣን የማሳደድ ተልዕኮ እንደሌለው፣ መንግሥትንም የሚተቸው የተጣመመው እንዲቃና፣ የተበደለው እንዲካስና ነፃነት እንዲጠናከር ካለው ቅን ፍላጎት በመነሳት መሆኑን ርዕሰ አንቀፁ ይገልጻል።

## ጉዳይ ሁለት

የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች እንከን የማይወጣላቸው እንዳይደሉ፣ ነገር ግን ስህተታቸው የሙያ ስህተትና ድክመት እንደሆነ፣ የመንግሥት ችግር ከሚከተለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አይዲዮሎጂ የሚመነጭ መሆኑና ይህ ርዕዮተ ዓለም ከራሱ ውጪ ሌሎች እንዲኖሩ የማይፈቅድ መሆኑ ነገር ግን በሌላ በኩል በአብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ በነፃው ፕሬስ የነፃነትና የዴሞክራሲ ጥማት መካከል ያለው ቅራኔ በመቀራ ረብና በመነጋገር ሊታረቅ እንደሚችል፣ የአገራችንን ችግር እኛው ራሳችን መፍታት እንደሚኖርብን፣ እንደምንችልም፣ ነፃው ፕሬስም ግዴታውን ማክበር እንዳለበት እንዲሁም መንግሥት ሕገ መንግሥታዊ ግዴታውን ሊወጣ እንደሚገባ በሁለቱም ወገን ያሉ ስህተቶች ሊታረሙ እንደሚገቡ ገልፆልናል።

ነፃው ፕሬስና ጋዜጠኞቹ ከአላስፈላጊ እንግልት መዳን እንዳለባቸው፣ መንግሥትም ከአላስፈላጊ ትችት (የውጭ መንግስታትን ትችት ጨምሮ) እንዲላቀቅ የብሔሮችና የሕዝቦች መብት እንዲሁም የሀገራችን ገፅታ እንዲከበር ማድረግ እንደሚያስፈልግ መጽሔቷ አቋሟን ገልጻለች። ለመሆኑ ጋዜጠኝነትና እውነት ምንድን ነው?

## ጋዜጠኝነትና እውነት

እንደ አዲስ ጉዳይ ገለጻ «ጋዜጠኛው እውነትን የማሳወቅ እንጂ ስልጣን የማሳደድ ተልዕኮ የለውም፤» ይህ በመርህና በሙያ ዲሲፕሊን ደረጃ ትክክል ነው። በተግባርም መሆን ያለበት ነው። የጋዜጠኝነት ሙያ እውነትን የማፈላለግ ተግባር ነው። ነገር ግን እውነትን የማፈላለግ ጉዳይ ሚዛናዊ ሆኖ የመገኘት ጉዳይም ነው፤ ሚዛናዊነት ከሌለ እውነት ማውጣትም፣ መፈለግም የለም።

ከእውነት ማፈላለግ ጎን ለጎን በእውነት ማፈላለግ ውስጥም ሚዛናዊነት ሊኖር ግድ ነው። ሚዛናዊ

ያልሆነ ዘገባ ጥቃት እንጂ ዘገባና ጋዜጠኝነት አይሆንም። ሚዛናዊነት በጎደለበት እውነትን ማሳወቅም፣ መፈለግም፣ የተጣመመን ማቃናትም አይቻልም። እንዲያውም ሚዛናዊነት በተጓደለበት እውነት ራሷ አደጋ ላይ ትወድቃለች፣ ትጣመማለች፣ ፍትህ ታጎድላለች።

ለምሳሌ አበበ የተባለ ሰውን መታሰር፣ ከሀገር መውጣት፣ በሕግ መጠየቅ ወዘተ. በሚዛናዊነትና በእውነት ማፈላለግ አንፃር ማየትና መረዳት ካልተቻለ የጋዜጠኝነት ዘገባ አደጋ ላይ ይወድቃል፤ በእዚህ ሂደት ለዘጋቢው እውነትን የማፈላለጉ ታላቅ ሥራ ወትሮም ቢሆን ሙያውና ዓላማው አልነበር፤ ከሆነ ዓላማው የሆነውን ጉዳይ በገደምዳሜ (ገደምዳሜን ከቀድሞዋ ፍትህ ኮረጅኩ፤ ይህ እውነት መናገር ነው)ያሳካ ይመስለው ይሆናል። ይህም ሆኖ በእዚህ አካሄድ የሕዝብና ለሕዝብ የሆነውን ሙያ ከስም በቀር በተግባር ማገልገል አይቻልም። ጋዜጠኛ የሚለውን ስያሜ ከውስጥ መላበስም አይሞከርም። ስለሆነም እውነትን ስንጠራት፣ ስለ እውነት ቆመንና እውነተኛ ሆነን ይሁን። ስለ ሃቅ ብዙ መናገር ሃቀኛ አያሰኝም።

ከዚህ አኳያም «የስደትም የሕግ ተጠያቂነትም ሰለባ ሆነዋል» ስለምንላቸው ሰዎች ምን ያህል እውነተኛ ጋዜጠኞች ነን ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል። በማንም ዜጋችን መታሰር፣ መጎዳትና መንገላታት (አጥፍቶም ቢሆን) የሚደሰት ካለ እርሱ የሰብዓዊነት እጦት ነው። ነገር ግን ሕግ ማክበርና ማስከበር አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ጋዜጠኛው ሙያዊ ኃላፊነቱን በሙያዊ ዲሲፕሊን በመመራት እንደሚወጣ ሁሉ በሕግ የተቋቋመ አካልም የተሰጠውን ሕጋዊ ኃላፊነት በአግባቡ የመወጣት ግዴታ አለበት፤ ከዚህ ሲያልፍ እርሱም የሙያ ተጠያቂነት ይኖርበታል።

ጋዜጠኝነት ግን ከእዚህ በላቀ ሁኔታ ኃላፊነት ይፈልጋል። ጋዜጠኛ ብዕር ስለያዘ መሣሪያ ከያዘ ጋር አይወዳደርም ብሎ «ቂሱን» የሚያወዳድር እውነት ፈላጊ ነኝ ባይ ጋዜጠኛ የዋህ ነው፤ ወይም ብዕርና ጦር መሣሪያን በቂመና ካልሆነ በቀር በግብር አልተገነዘባቸ ውም ማለት ነው። ለሙያ ዲሲፕሊኑ ያልተገዛ ብዕርና ጋዜጠኝነት ከአጥፊም በላይ አጥፊ ስለመሆኑ «የሁቱና ቱትሲ ታሪክን እያነሱ ማስረዳት አያሻም።»

ስለ 1997 ዓ.ም ሰሞን የጋዜጠኝነት መስፋፋትና የህትመት ቅጂ መብዛት የሚያወራ ተቺ በእዚያን ወቅት አንዱን ብሔር በሌላው ላይ ለማስነሳት ያልተቋረጠ ቃታ ሲስብ መቆየቱን ዘነጋሁ ቢል አይታመንም። ስለዚህም ቅጂውን ብቻ ሳይሆን አስተሳሰቡን መቁጠር «አብዮታዊ ዴሞክራሲያውያን ካላሰኘ በስተቀር» አስፈላጊ ነው። እውነት ማፈላለግ ማለት እንዲህ ዓይነት ሚዛናዊ መሆን ማለትም ጭምር ነው።

በግልፅ ለመነጋገር ለደፈረችው አዲስ ጉዳይ ምስጋና ይግባትና በመጽሔቷ ሽፋን ያወጣቻቸውን ምስሎች በድፍኑ «በነፃ ፕሬስ» ስም ጠቅልላ የነፃ ፕሬሱ አርበኞችና ተሳዳጆች ለማድረግ መሞከሯም አስገራሚ ነው። እውን በምስሉ የተገለፁ ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብት ተጠቅመው፥ (ሕጉን እንኳ ትተን) የጋዜጠኝነት ሙያና ዲሲፕሊንን አክብረው ሲሰሩ ነበርን? በፖለቲካ ብቻ ሳይሆን በጥላቻ ፖለቲካ የተጠመዱ የነበሩ ስለመሆናቸው ለአዲስ ጉዳይ ይጠፋታል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው።

ነፃ ፕሬስ ከየትኛውም የአስተሳሰብ ጫና ነፃ ሆኖ ነፃ ሃሳብንና አመለካከትን በእኩልና ፍትሐዊ መንገድ ማሰራጨትን እንጂ በነፃነቱ በተከፈለ ዋጋ የአንድ ቡድንን፣ ወይም የራስ የከረረ ፍላጎትን ሕግን ባላከበረ ሁኔታ በኃይል ለማስፈፀም በነፃነት ስም መተንተን፣ በሌሎችም ላይ ጫና መፍጠር ማለት አይደለም። አዲስ ጉዳይ እንዳለችው ጋዜጠኝነት እንደ ሌሎች ሙያዎች ሊታይ የማይችል ቢሆንም ለሕዝብ መብት መከበር ዝቅተኛ ግምት የሚሰጥ ነው ማለትም አይደለም። ስለዚህም አርአያ የምናደርጋቸውን ሰዎች በግል መውደድ፣ ማክበርና ማወደስ መብታችን ቢሆንም እውነትን መደፍጠጥ ግን ኢ ሥነምግባራዊና አስተዛዛቢ ነው። እናም ሚዛናዊ እንሁን።

## የስደት ቀብድ ወይስ...?

አዲስ ጉዳይ ስደትና እንግልት ይቁም ስትል በገለጸችበት ርዕሰ አንቀፅ ስለ ነፃ ፕሬስና ነፃ ጋዜጠኝነት ነግራናለች። ለመሆኑ በሙያው ስም አንድ ህትመት የመሠረተ ቡድን ነፃ ነኝ ስላለ ብቻ በተግባር ነፃነቱን ያረጋገጠ ነውን? ለራሱ በአስተሳሰብ ነፃ ያልወጣ «ጋዜጠኛ» ሌላውንስ እንዴት ነፃ ሊያወጣ ይችል ይሆን? ቀድሞ የራሱን ነፃነት ያላረጋገጠ ጋዜጠኛ ነኝ ባይና የህትመት ውጤት

ስለ ነፃነት ለመናገር ከቶ እንዴት ይቻለዋል? ህትመቶቻችን ስለነማን ወግነው ነው የሚከራከሩት? በእውነት የመመርመሩ አቅምና ፍላጎት አላቸውን? ከምንም ነገር በፊት ይህን በቅጡ መረዳት ይገባል።

ይህን ስል ሁሉም ተመሳሳይ ፈለግ ያላቸውና አረማመዳቸው አንድ የሆነ ነው ማለቴ አይደለም። በአንዳንድ የግል ህትመት ውጤቶች ሳይቀር የመንግስት ወገንተኛ ነው ተብሎ የሚገለጸው የሕዝብ መገናኛ ብዙኃንና የህትመት ውጤት ስሙ ለሚጠራበት መንግሥት እያገዘና እየወገነ ነው የሚል እምነት የለኝም። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መንግሥት ማለት ሕዝብ ነው ብለን ከበየንን አሁን ያለው የሕዝብ መገናኛ ብዙኃን ለመንግስትም፥ ለሕዝብም እያገዘና እየወገነ አይደለም እላለሁ።

እንደ እኔ ሚዲያው እውነትን በማፈላለግ ተግባር አብዝቶም፣ ሳያበዛም የተጠመደ አይደለም። አንዳንድ ጠንካራ የግል ህትመት ውጤቶች እንዳሉ ሁሉ በነፃ ጋዜጠኝነት ስም ተስፋ መቁረጥና ሞት ከመዝራት በቀር በተጨባጭ መረጃና ማስረጃ ላይ ተመርኩዘው በማይተቹ፣ በማያጋልጡ፣ በሚያጥላሉና በሚጨፍኑ የህትመት ውጤቶች ሊነገር የሚችል ኃጢአት ግን የለውም፤ እንዲህ ዓይነቶቹ ነፃ ነን ባዮች፣ የሀገራችን ጉዳይ ያሳስበናል ብለው በቃል ምንም ቢሉም በተግባር የጨዋታው ሜዳ ላይ አላየናቸውምና ሕጉን አክብረው የሚንቀሳቀሱትን የግልና የሕዝብ ፕሬሶች ለመተቸት አቅም የላቸውም።

ይሁንና የሕዝብ መገናኛ ብዙኃኑ የመንግሥትን ስኬት ለመግለጽ የሚደክመውን ያህል ድክመቱን ለመንግሥት አይነግረውም፤ ስኬቱንም ቢሆን ያለ ድካም ለማቅረብ የሚጻዳ እንጂ የሕዝብ አደራና ኃላፊነት አለብኝ ብሎ እውነትን ለማውጣት ሲተጋ ብዙም አይታይም፤ እዚህም ላይ ቢሆን ጭፍን መሆን አልፈልግም። ነገር ግን ፕሬሱ ራሱን ነፃ ነኝ ብሎ በቃልና በመፈክር ከመግለፅ ባለፈ ወገንተኝነቱ ከእውነትና ከሃቅ ጋር መሆኑን በተጨባጭ ሊያረጋግጥ፣ ነፃ መሆኑንም ሊያሳየን ይገባል።

ነፃነቱ በውስጡ ያለ ጋዜጠኛ ሕግና ሕጋዊነት «እውነት መሆኑን» ያውቃል፤ ሕግ ያከብራል፣ ሕግ እንዲከበር ይሠራል። ሕግ አቅም ካጣ የጉልበተኞች ሰለባ እንደሚሆን፥ ለሕገ ወጦች ጥቃት

እንደሚጋለጥ ይገነዘባል። ስለሆነም ለሕግ መከበር አርአያ ሆኖ ይሰራል።

ሕግን ማክበርና ለሕግ መገዛት ሲባል የሕጋዊ ተቋማትን ሰውነት ወይም ተቋማዊ ሰብዕና ማክበር ማለትም ነው። ለውሳኔዎቻቸው መከበር መገዛት ማለትም ጭምር ነው፤ በአንፃሩ በሕገ መንግሥታዊ መብትና ነፃነት ተጠቅሞ ውሳኔዎቻቸው ስህተት ካለበት በመሰለኝ ሳይሆን በመረጃ ላይ ተመስርቶ መሞገት፣ ማጋለጥና እንዲስተካከል ማድረግ ይገባል።

በነገራችን ላይ ያጋደሉ እና የተዛቡ (Tilted & Slanted) ዘገባዎችን በተደጋጋሚ የሚያስኮመኩሙን አንዳንድ ህትመቶች ስለ ነፃ ጋዜጠኝነትና ስለ እውነት በምን ሞራል እየነገሩን እንደሆነ ለማወቅ በጣም ያዳግታል። ጋዜጠኝነት የሞራል ጥያቄም አለበት። መስዋዕትነቱ በግል ስምና ዝና እንዲሁም ቡድኖች የግል ጥቅም ከማትረፍ ሳይሆን ለሙያ ሥነ ምግባርና ዲሲፕሊን ከመገዛት ይመነጫል።

የሙያውን ክብር ተጎናፅፈው በጨበጡት ብዕር ያሻቸውን ሲዘሩ የሚውሉ ጸሐፊያን ጋዜጠኞች ናቸው አይደሉም ለማለት ብዕራቸውን በጋዜጠኝነት ሙያና ዲሲፕሊን መመዘንና መመርመር ያስፈልጋል። ይህን ባላገናዘበ ሁኔታ ይሁነኝ ብሎ በሙያው ስም የተለየ ጥቅምና ፍላጋ መሻት ጋዜጠኝነትን ለግል ብልፅግና መሸጥ ነው የሚሆነው።

የጋዜጠኝነትና የነፃ ብዕር እስትንፋስ ህያውነት የሚናፍቃቸው ወገኖች በቅድሚያ ሊመረምሩ የሚገባው የሕግ ተጠያቂነት ያረፈባቸውና የሚያርፍባቸው ሰዎች እውነት በሙያቸው ማለትም ከጋዜጠኝነት ጉዳይ ጋር በተያያዘ በመፃፋቸው ነው ወይ የሕግ ተጠያቂነት ያረፈባቸው? የሚለውን ነው።

ይህን ማለቱ አሳሪ ለሚባለው መንግስትና ታሳሪ ለሚባለው ሰው መብት ብቻ ሳይሆን የገፅታዋ ጉዳይ ከአንገትም ይሁን ከአንጀት ለሚያሳስበን አገራችን እንዲሁም ባሻን ጊዜ ብቻ 80 መሆኑን ስለምናውቀው ብሔር ብሔረሰቦቻችን ጥቅምና እድገት ይበጃል። እንደተባለው ዴሞክራሲን በመለማመድ ላይ ነን ብለን ብዙ ጊዜና ወጪ እንዳናባክንም ይረዳናል።

ዜጎች በጋራ ጉዳዮቻቸውና በሀገራዊ ጥቅሞቻቸው ላይ የጋራ አቋም እንዲይዙም ያደርጋል። አለያ

አድካሚውን እውነት የማውጣትና የመቆፈር ሥራ የመስራት አቅም ሲያንስ የአቋራጭ መንገድ ለማበጀት የሚጥሩትን ሁሉ ከእውነታ በመሸሽ በሚሰሩት አስጠርጣሪ ጉዳይ በምንም መልኩ የሕግ ተጠያቂነት እንዳይኖርባቸው የጋዜጠኝነት ካባ የምናለብሳቸው ከሆነ የዴሞክራሲና የነፃነት፣ የነፃ ሃሳብም አደጋ ይደርሳል። ይህን እያሰቡ መንቀሳቀስ ለሌላው ባለሙያ ክብር አለመስጠትና ከሕግ በላይ ለመሆን መከጀልም በመሆኑ ተቀባይነት የሚኖረው አይሆንም፤ ምንአልባትም ለራስ የስደት ቀብድ ለመክፈል መፈለግ ካልሆነ በቀር።

## መተንፈስም፣መተርተርም በሚቻልባት ሀገር ታፈንን

ጋዜጠኞች ፖለቲከኞች የማይሆኑት በሙያቸው ለአንዱ ፖለቲካ ፓርቲ አያዳሉም፤ ወይም አይወግኑም ከሆነ ትክክል ሊሆን ይችላል፤ አባባሉ ጋዜጠኞች ፖለቲካዊ አቋም የላቸውም የሚል ከሆነ ግን ስህተት ነው።

ጋዜጠኞች እንደማንኛውም ዜጋ የፈለጉትን የፖለቲካ ፓርቲ የመደገፍ መብት አላቸው። ልዩነቱ በሚሰሩት ሙያ አንድን ወገን ለመጥቀም በሚል መንፈስ አይሰሩም የሚለው ነው። ይህ ትንታኔ ሊያስማማ ይችላል። ነገር ግን ልዩነቱ የሚመጣው አዲስ ጉዳይ ከዚህ ቀጥሎ ካራመደችው አቋም ጋር ተያይዞ ነው። ይህም መንግሥት በጋዜጠኞችና በፖለቲከኞች መካከል ስላለው ልዩነት እንደማያውቅ ወይም አውቆ እንደማያውቅና ጋዜጠኞችን የፖለቲካ ጥቃት ኢላማ የማድረግ ፍላጎት አለው የሚለው ላይ ነው።

እውነት እንነጋገር ከተባለ በእኛ ሀገር ማን ጋዜጠኛ፣ ማንስ ፖለቲከኛ እንደሆነ እንኳንስ ሕግን የማስከበርና ሀገር የማስተዳደር ኃላፊነት ያለበት መንግሥት ቀርቶ ሕዝቡ አያውቀውም? ነው ወይንስ በይፋ ፓርቲ ስላላቋቋመና ምርጫ ቦርድ ስላላወቀው ሙያውን ላልተገባ ተግባር አላዋለም ነው?

ለነገሩ ጉዳዩን አዲስ ነገር ወዳልሆነ አቅጣጫ ወሰደችው እንጂ ችግሩ እርሱ አይደለም። ማንኛውም ሰው የመሰለውን ሃሳብና አመለካከት የመደገፍ፥ የማንፀባረቅ መብት እንዳለው በማያሻማ ሁኔታ በሕገ መንግሥቱ ሰፍሯል። በእዚህ ሃሳብን የመግለጽ መብት በመጠቀምና በመደራጀት ያሸነፈ ፓርቲ

የመንግሥትነት ድርሻ ሲኖረው እንደ መንግሥት ፖሊሲውን ለማስፈፀም የሚደረገው ጥረት ፓርቲያዊ ጉዳይ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። ችግሩ ግን አሁንም እርሱ አይደለም።

አዲስ ጉዳይ እንዳለችው በነፃ ጋዜጠኝነት ስም የነገ የቪዛ ቀብድ ለክፉም ለደጉም ማስቀመጥ የሚሹ በሙያ ሥነ ምግባራቸው የነጠፉ አንዳንዶች ከሙያም ከሰብዓዊነትም ፈፅሞ የማይጠበቅ እጅግ ነውረኛ ተግባር በተደጋጋሚ እየፈፀሙ መንግሥትን እስረኝ በማለት ሲማፀኑ የተስተዋለበት ሁኔታ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ይልቅ በእነዚያ ጊዜያትና አሁንም ጭምር የመንግስት ትዕግስትና ሆደ ሰፊነት በዝቷል የሚሉ አሉ፤ ብዙዎቹ ግን የመንግሥትን ዝምታ ወደውታል። ለምን ቢባል ሕዝቡ ማን ምን እንደሆነ አንጥሮ አውቆታልና።

አንባቢው የጠራውን የፕሬስ ውሃ ከምንጬ እስኪጠጣ ድረስ በደፈረሰው ማዝገም ግድ እንደሆነበት ያላወቁ ባለ አቋሞች ሕዝቡን እነርሱ በጋዜጠኝነታቸው እያረኩት፣ እየተፈለጉና እየተነበቡ መሆኑን እንጂ አማራጭ አጥቶ ያማተራቸው መሆኑን መገንዘብ ተስኗቸዋል። ለእነርሱ ተመልካች ዓይንና ሰሚ ጆሮ የበሬ ወለደ ተራኪዎቹ ሂዩማን ራይትስ ዎችና አምነስቲ ኢንተርናሽናል እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም።

የእነርሱ ሕግን ተፃርሮ አሰላለፍን ከጠላት ጋር ጭምር አሳምሮ የመንቀሳቀስ አዝማሚያ ለህዝቡ የሚሰጠውን ምልክት ፈፅሞ አልተረዱትም፤ ለእነ ማን ምን እያስፈፀሙ እንዳለ ማወቁም አልገባቸውም፤ ዳሩ «አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም» እንደሚባለው አውቆ የተጨፈነ እንዴት ይህ ሊታየው ይችል ይሆን?

ቅልጥ ባለ ነጭ አደባባይ አሜሪካና ዓለም አሸባሪ እንዳሉት ቢን ላደን አፈ ቀላጤ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ምክር ቤት በይፋ አሸባሪ መሆኑን ላወጀው ግንቦት ሰባት ይፋዊ አቀንቃኝ መሆናቸውን ያወጁ ግለሰቦችን፣ ዕለት ዕለት ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ የሚቋምጡና የሚያስተባብሩ ቡድኖችና ግለሰቦችን ሕግ አክብሩ በሕጋዊ መንገድ ተንቀሳቀሱ ብሎ መተቸት ባይፈለግ እንኳ በጋዜጠኝነትና በነፃ ፕሬስ ካባ «መንግሥት ለእዚህ ምን መልስ አለው?» ብሎ ሊጠየቅ አይገባም፤ መልሱ ያለው ጠያቂው ጋ ነውና። በነገራችን ላይ ከራሱ ከአዲስ ጉዳይ ገለፃ

መንግሥት የዜጎቹ መታሰር ያረካዋል ብሎ እንደማያምን ተረድቻለሁ። ይሄ ትክክል ነው። ታሰሩ የተባሉም ሆኑ፣ የተሰደዱ ተብለው የተጠቀሱ ዜጎቻችን ናቸው።ሕጉን በጠበቀ ሁኔታ ጉዳያቸው ቢታይ ክፋትም የለውም።

ነገር ግን ከመነሻው በተያዘው የአዲስ ጉዳይ አስተሳሰብ ስለ ነፃ ፕሬስና ነፃ ጋዜጠኝነት መስበክ እንዴት ይቻላል? ነው። «ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ» ይሏል ይኸው ነው። አዲስ ጉዳይ ግለሰቦቹ በይፋ ምን እያከነወኑ እንደሆነ አላውቅም ሊል አይችልም፤ ይልቅ ለመናገር አልፈልግም እንጂ።

የስደቱ ምንጭና የመሰደድ ፍላጎት በምን እንደሚገለፅ ግን ሊነገረን አይገባም። በኢትዮጵያ በፖለቲካ ጉዳይ አቋም በመግለፁ የሚታሰርም፣ የሚሰደድም አይኖርም፤ የለምም። የእዚህ ማሳያው እናንተ ናችሁ ብሎ መግለጽ ድፍረት ስለሚሆን አልለውም። ግን ይህን እውነት መመርመር ያላስቻለው ጭፍንነት ከምን መነጨ? ከነፃ የጋዜጠኝነት አስተሳሰብ? ከነፃ የፕሬስ አቀንቃኝነት? ሀገርንና ብሔር ብሔረሰቦችን አብዝቶ ከመውደድ? ወይስ ከምን?... አሁንም በድጋሚ አንዳንዶች በነፃ ፕሬስ ስም ታፈንን በሚል የባንክ አካውንት በቃላት ለስደት ቀብድ ከፍለው፣ ከመተንፈስ በላይ መተርተር በሚቻልባት ሀገር የፕሬስ ነፃነትን ጥያቄ ውስጥ ለመክተት መሞከራቸው አስተዛዛቢ ነው።

## ክፍል ሁለት

የአዲስ ጉዳይ መፅሄት ሁለተኛ «ጉዳይ» ይህን ይመስላል።

- የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች እንከን የማይወጣ ላቸው እንዳይደሉ፣ ነገር ግን ስህተታቸው የሙያ ስህተትና ድክመት እንደሆነ፤
- የመንግሥት ችግር ከሚከተለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አይዲዮሎጂ የሚመነጭ መሆኑና ይህ ርዕዮተ ዓለም ከራሱ ውጪ ሌሎች እንዲኖሩ የማይፈ ቅድ መሆኑ ነገር ግን በሌላ ገለፃ ደግሞ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፤በነፃው ፕሬስ የነፃነትና የዴሞክራሲ ጥማት መካከል ያለው ቅራኔ በመቀራረብና በመነጋገር ሊታረቅ እንደሚችል፤
- የአገራችንን ችግር እኛው ራሳችን መፍታት እንደሚኖርብን፣ እንደምንችልም፣ ነፃው ፕሬስም ግዴታውን ማክበር እንዳለበት እንዲሁም መንግሥት ሕገ መንግሥታዊ ግዴታውን ሊወጣ

እንደሚገባ፥ ከአላስ ፈላጊ ትችት (የውጭ መንግሥታትን ትችት ጨምሮ) በእዚሁ የሚላቀቅ መሆኑ በሁለ ቱም ወገን ስህተቶች ሊታረሙ እንደሚገባም ገልፆልናል።

በነገራችን ላይ ይህ የርዕሰ አንቀፅ አቋም «በመንግስት ለእዚህስ ምን መልስ አለው?» ጥያቄ ውስጥም በስፋት የተብራራና የተስተጋባ ነው። በመሆኑም በርዕሰ አንቀፁ የሰፈረው ሃሳብ ከእዚህኛው ጋር በጉዳይም ሆነ በአስተሳሰብ ለውጥ የሌለው በመሆኑ እዚህና እዚያ እየረገጥን መመልከቱን እንቀጥላለን።

## የሙያ ስህተት ወይስ...?

መጽሄቱ የመንግስትን አውቆ ተሳሳችነት አጉልቷል፤ እንዲያውም የጠቅላይ ሚኒስትሩ የ15 ዓመት የዴሞክራሲ ልምድ ጉዳይ ገለፃ ነው ባለው ሃሳብ ላይ ሊከተለው የፈለገውን የራሱን መንገድ መርጧል። የእነ አሜሪካ ዴሞክራሲ ከ200 ዓመታት በላይ ልምድ አለው፤ እኛ በዴሞክራሲ ብዙ መስራት አለብን፤ በሂደት እያሻሻልን መጥተናል፤ ዴሞክራሲ በሂደት እንጂ በነፀብራቅ ፍጥነት አይጎለብትም የሚል የሁልጊዜም ሃሳብ ባለው መንግስትና በጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ የተነሳው ሃሳብ በአዲስ ጉዳይ አተረጓጎም ሌላ መስሎ ቢቀርብም ለእዚህ ፅሑፍ አንባቢ ግን ግልፅ ነው ተብሎ ይታሰባል።

መፅሄቱ ምን አለ የሚለውን መተንተኑ ሳያስፈልግ ሀገራችን ካለፈው ጊዜና የረጅም ልምድ ባለቤት ከሆኑ ሀገሮች በተሻለ ፍጥነት ወዳሰበችው መጓዟ አይቀሬ እየሆነ መምጣቱ በተጨባጭ እየታየ ነው። በመፅሄቱ ገለፃ መሰረት የኢኮኖሚ እድገታችንና የልማት ፍጥነታችንን የአውሮፓ አገራት ማወደሳቸው መገለፁን አስረጂ አድርጎ ማቅረብ አያሻም።

ስለ ዴሞክራሲ ስናነሳም እነ አሜሪካ የወቅቱ ዓለማዊ ሁኔታ በፈቀደላቸው መልኩ ሲጓዙ መሰንበታቸው ይታወቃል፤ ነገር ግን የአሜሪካንን ዴሞክራሲ እስከአሁን ድረስ የሚተቹ ወገኖች ጭምር በስፋት በመኖራ ቸው የዴሞክራሲ ትርጉም ምንድን ነው ብሎ መጠየቅ ጊዜ ሊወሰድ ይችላል። ስለሆነም ግልፅ የሆነው ሃሳብ ዴሞክራሲ በአስተሳሰብ እድገት፣ በሃሳብ ላይ በተመሰረተ ውይይትና ክርክር፣ በሰላምና ልማት መጎልበት የሚመጣ ነው የሚለው ነው። የጠቅላይ ሚኒስትሩም

ሃሳብ ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ነው።

ለዴሞክራሲ መጎልበት ሚዲያው ወይም ፕሬሱ መተኪያ የሌለው ሚና እንደሚጫወት ግልጽ ነው። ፕሬሱ ሚና አለው ሲባል ጠረኛ ነው ወይም ጦር አዝማች መሆን አለበት ማለት አይደለም። ጦር አውርድ ተለማማኝ ተግባር፤ ልማት፣ እድገትና ከድህነት መውጣት በእጅጉ ለሚያስፈልጋት፣ የድህነት መጥፋት ጥያቄ የህልውና ጉዳይ ለሆነባት ሀገር አደገኛ ነው።

ዴሞክራሲን በቃል ደረጃ ብቻ ከእነ ሂዩማን ራይትስ ዎችና አምነስቲ ኢንተርና ሽናል ወስደን ህዝባችንን ከዘነጋነው አደጋ ነው። ህዝቡ ዴሞክራሲን የሚፈልገው በወረቀት ላይ ብቻ ሳይሆን በተግባር ነው። በወረቀት ላይ የተፃፈው ህግ ተግባራዊ እንዲሆን ይሻል። ሃሳብ የለውጥና የእድገት መሠረት በመሆኑ ለእዚህ የሚሆን ሰላምና መረጋጋት ይፈልጋል። ይህን የሚያስቀጥሉ ለትን ፕሬሶች አጥብቆ ይሻል። ደሃ መሆኑን እያወቁ ከድህነት ለመውጣት የማይረዱት፣ ይልቁንም የልማት ርብርብ እንዳያደርግ የሚያሰናክሉትን የስም ፕሬሶችና የስም ተቃዋሚዎችን ጠንቅቆ ያውቃቸዋል። ልማትና እድገት ጠምቶት ከሌለው ሳንቲም ላይ እንደምንም ተጣጥሮ ቦንድ ቢገዛ ጥርጣሬ ውስጥ የሚከቱት ዓለም አቀፍ የፀረ ልማት ዘመቻ በሚመስል አኳሃን ዓለም በገሃድ እያየው ላለው የግድብ ግንባታ የሚደረግ የቦንድ ግዥ ለማጨናገፍ የሚራ ወጡ ቡድኖችን የማይተቹ፤ እንደሌሉም የሚቆጥሩ ህትመቶች ደርሶ ለህዝብና ለሀገር ተቆርቋሪ ሲሆኑ ያስተዛዝባል። ነፃነታቸውን በራሳቸው ተገፍፈው ነፃ ነን ሲሉም ይገር ማል። በእዚህ ረገድ የሚወነጨፉ ተግባራትን መኮነን የ«አብዮታዊ ዴሞክራት» ነው በሚል የርዕዮተ ዓለሙን ፍልስፍና ባልተረዳ አንደበት ነፃነትን መስበክስ እንዴት ይቻል ይሆን?

ስለዚህም ነፃነትን በቀዳሚነት ማወጅ የሚያስፈልገው በራስ ህሊና ነው፤ ኢህአዴግን ወይም ሌላ የጥፋት አራማጅን ፈርቶ መሃል ቤት መዋለል ነፃነት አይደለም፤ ይልቅ አቋም አልባነትና ነፃ አለመውጣት ነው። ነፃ አሳቢዎች ጥሩውን ጥሩ፣ መጥፎውን መጥፎ ለማለት ይደፍራሉ። ፖለቲከኞችም የራሳቸ ውን አቋም ትክክል ነው ብለው(ፈራጁ ህዝብ መሆኑ ይታወቅ) የሌላው ትክክል ያልሆነበትን መንገድ ይተቻሉ።

ጋዜጠኞች ለየትኛውም ሳይወግኑ ስለ እውነት ይሞግታሉ፤ ስለ ህዝብ ጥቅም ይሰራሉ። እውነት ከኢህአዴግ ጋር እስከአለ ድረስ እውነቱን መደገፍ፣ አለያም ከሌላው ቡድን ዘንድ እስከአለ ድረስ የእርሱን አስተሳሰብ ትክክል ነው ብሎ መግለፅ መብት ብቻ ሳይሆን የሙያ ግዴታ ነው። ይህን የሚተገብሩ የነፃ ፕሬስ ሰባኪያን ምን ያህል ናቸው? የማይተገበር ሃሳብ እንደ መደርደሪያ ላይ መፅሃፍ ነው። ስለዚህም ቃላችንና ተግባራችን እንዴት ነው ብለን ወደ ራሳችን መመልከት ይኖርብናል።

የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች ስህተት የሚፈፅ ሙት ከሙያ ጋር በተያያዘ ብቻ አይደለም። የሙያ ላይ ስህተቶችን በሚፈፅሙ ጋዜጠኞች ላይ መንግሥትና ሕጉ ምን ያህል እንደ ሚደግፏቸው ግልጽ ነው። በተፃፈ ሕግ እንደሚያስጠይቅም በትልቁ የሽብርተኝነት ወንጀል መሰማራት ከጋዜጠኞች በስተቀር ያስጠይቃል የሚል ሕግ እንዲወጣ ፍላጎት ካለ ግን ሕገ መንግሥቱን መቀየር ያስፈል ጋል።

የዜጎችን ደህንነት መጠበቅና ህግን ማስከበር ዓላማው ያደረገ መንግስትን በተፃፈው የህግ ጉዳይ እየተገዳደሩ፤ የፀረ ሽብርተኝነት ህጉን አክብሩ ማለት ያልቻሉ የነፃነት ሰባኪያን እንዴት ሚዛናዊ መሆን ይችላሉ። ይልቅ ህጉ ችግር ካለበት ችግሩ እንዲቀረፍ በመጠየቅ እስከዚያው ግን አክብሮ መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ እንዴት መረዳት ይሳናል የሚል ጥያቄ ያስከትላል።

## ከፀረ ዴሞክራሲ ወደ ዴሞክራሲ

ሁለተኛው ጉዳይ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፅንሰ ሃሳብ ነው። ይህ ጉዳይ የነፃነት ሰባኪያን እንሁን የሚሉት ወገኖች ሁለተኛ ስህተትም ነው። አብዮታዊ ዴሞክራሲ በትርጉም ካልነበረ ዴሞክራሲ ወደ ዴሞክራሲ መሸጋገር ነው። በእዚህ አገላለጽ የዴሞክራሲ አዲስ ለውጥ ነው። ይህ አስተሳሰብ ሕዝባችን ፍፁም አምባገነን በነበሩ ሥርዓቶች ሲደርስበት የነበረውን የግፍ አገዛዝ በማስወገድ ዴሞክራሲ ያዊ ሥርዓት ለማስፈን አቅጣጫ የተያዘበት ነው።

በእዚህ የአስተሳሰብ ማዕቀፍ ውስጥ በመሆን ለአገሪቱና ለሕዝቡ የተሻለ አማራጭ የሚያመጣው የሕዝቡን መሠረታዊ ጥያቄ በማስጠበቅና በማስከበር የሚያስቀጥለው የትኛው ነው? የሚለው

ታይቷል፤ ከእዚህም አንፃር አዋጪው የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት አስተዳደር መሆኑ ተሰምሮበታል።

ለነገሩ የገበያ አክራሪዎቹ መንግሥታት በኢኮኖሚ መዋዥቅ ክፉኛ በተጠቁበት ጊዜያት የእኛ አማራጭ አስፈላጊና ተመራጭ መሆኑን ሳይወዱ በግድ ተቀብለውታል። የእኛ አገር ግን ከምንም ተነስቶ አልተገበረ ውም። ህዝቡ ልማት ይፈልጋል፣ ልማቱም ያለ ዴሞክራሲ አይመጣም።

በእዚህም መሠረት በሁሉም የሀገራችን ፖሊሲዎች ሳይቀር ልማትና ዴሞክራሲ የማይነጣጠል መሆኑ፤ የሀገራችን ልማት ከእዚህ ውጪ የማይሳካ መሆኑም ተገልፆ፤ ተግባራዊም ተደርጎ ውጤት አግኝተናል። በሀገራችን ባለፉት ተከታታይ ስምንት ዓመታት የተመዘገበው የ 11 በመቶ አማካይ እድገት ዓለም የመሰከረለት ፈጣንና አንፀባራቂ እድገት በስብከት አልመጣም፤ በተግባር እንጂ። ስለዚህም የርዕዩተ ዓለሙን መነሻ በመሳትና በመኮነን በሌላም በኩል እርሱኑ አስተሳሰብ ደግፎ የሃሳብ መታረቅ መፍጠር ይቻላል ብሎ መግለፅ አብሮ አይሄድም። ይልቅ በሃሳብ አዲስ ነገር መፍጠር በመቻሉና ካለፈው ጊዜ የተሻለ ሁኔታ በመፈጠሩ የተገኘ ልማትና እድገት ነው።

## የጋራ ችግርን በጋራ የሚፈታ አስተሳሰብ

የአገራችንን ችግር መፍታት ብቻ ሳይሆን ልማታችንን ራሳችን ማፋጠን እንደምንችል የተግባር ምስክሮቹ እኛው ነን።የታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴው ግድብ ግንባታ ጉዳይ ከሃሳብ ጥንስሱ በዘለለ ወደ ተግባር ሳይገባ በፊት የጋራ አቋም ይዘን ወደ መሰባሰቡ የሄድንበት፤ የ 1997 ግርግር ተከስቶ የሕግ ተጠያቂነት ያለባቸው ሰዎች በፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ ከተሰጠባቸው በኋላ በይቅርታ መፍትሄ የተሰጠበት፤ አገራችን ላይ የወረራና የሽብርተኝነት አደጋ በአንዣበበበት ወቅት ለጥቃቱ ተመጣጣኝ ምላሽ የሰጠንባቸው ወቅቶች የውስጥና የጋራ ችግሮቻችንን ራሳችን መፍታት እንደምንችል ያሳየንባቸው አጋጣሚዎች ናቸው።

በአንፃሩ እነዚሁ አጋጣሚዎች የትኛውም የውጭ ሃይል የሀገራችንን ሉዓላዊነት መዳፈር እንደማይችል፥ እጃችንን መጠምዘዝም ጭምር ሊሞከር እንደማይቻል የታሪካችንም የማንነታችንም መገለጫ መሆኑን ያሳየንባ ቸው አጋጣሚዎች ናቸው። ስለዚህም አዲስ ጉዳይ እንዳለችው

ችግሮቻችንን መፍታትና መወያየት ያለብን እኛው ነን፤ ይህ በጎ ባህልና ሃሳብ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል።

ነገር ግን የነፃ ፕሬስ ተዋንያን ነን የምን ልም ወገኖች አጀንዳችን ምንድን ነው ብለን ራሳችንን እንጠይቅ? ሃሳብ ውይይት እስከተካሄደበት ድረስ በደፈናው የሚያራርቅ ነው ተብሎ ሊፈረጅ አይችልም። ሆኖም ፅንፍ ተይዞ፣ ሀገራዊ የሆነ የጋራ ጥቅም ላይ መግባባት ጠፍቶ፤ የራስን ነፃነት በራስ ህሊና ማወጅ ካልተቻለ መወያየት እንዴት ይቻላል? ወደ ሌላው እንለፍ...

በመፅሄቱ እንደተገለፀው የመንግሥት ሆደ ሰፊነት ከእዚህም በላይ ቢሆን ጥሩ ነው። ይህም ሕዝቡ እያንዳንዱን ሁኔታ በበለጠ ለማየት እድል ይሰጠዋል። ቢያንስ አዲስ ጉዳይ በእዚህ ሃሳብ ላይ ምክንያታዊ ለመሆን መሞከሩ ጥሩ ነው ያሰኘዋል።

አዲስ ጉዳይ በሕገ መንግሥቱ መከበር ዙሪያም የሰነዘረችው ሃሳብ አለ፤ ሕገ መንግሥቱ መከበር አለበት። ይሄ የማያሻማና ትክክለኛነቱም የማያጠያይቅ ነው። ሕገ መንግሥቱ መከበር ያለበት ግን በሁሉም ወገን ነው። አንዱ ስላላከበረ ሌላው ይጥሰዋል በሚል እሳቤ ሳይሆን እንደ ፕሬስ ሕገ መንግሥቱን ማክበርና ማስከበር ቀዳሚ ልምዳችን እንዲሆነን ያስፈልጋል።

ያለ ሕገ መንግሥቱ መከበር ዋስትና የለንም፤ የመፃፋችን ብቻ ሳይሆን የመኖራ ችን፤ እንደ ሀገርም አንድ ሆነን የመቀጠላችን እጣ ፈንታ በህግና ህጋዊነት መከበር፤ በተለይም የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ በሆነው የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የቃል ኪዳን ሰነድ ላይ የተመሰረተ ነው።

ሕገ መንግሥቱ የሕዝቦች የጋራ ሃሳብ ነው፤ ቃል ኪዳን ነው፤ ጥቅማቸውም ነው። እርሱን በመፃረር የተለያዩ የሽብር ወንጀሎ ችን የሚፈፅሙ አካላት በየትኛውም የሙያ ሽፋን ቢከለሉ ከተጠያቂነት አያመልጡም። በአገራችን ሕግና ሕገ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትሩም፤ ሌላውም ዜጋ እኩል ነው። ጋዜጠኛውም፣ ዶክተሩም፣ ነጋዴውም ... በአንድ የራሱ ሕግ የሚመራ፤ ለሕጉ መከበርም የሚታገል ሊሆን ይገባል ይህን ሲያደርግ ግን በሰላማዊ ሁኔታ፣ ያለ ኃይልና ጫና መሆኑን ይገንዘብ። የአስተሳሰብ ነፃነትና ዴሞክራሲ ማለት ይኸው ነው። አለያ ብዕርና ጠብመንጃን ያለ ስፍራው በማወዳደር አሸባሪነት ማለት ጦር ሜዳ ላይ ጦርነት ማወጅ ነው ብሎ መግለጽ ስለ ሽብር ወንጀል

ተግባራት «ሀ ሁ» አለማወቅ ነው።

በአጠቃላይ የአገራችንን የረጅም ጊዜ ጉዞ ስናይ ሃሳብን በነፃ የመግለጽ መብት የፕሬስ ነፃነትም ጉዳይ ተግባራዊ የሆነው አሁን ባለንበት ሥርዓት ነው። ሕገ መንግሥ ቱን ጨምሮ የመረጃ ነፃነት ሕጉ የእዚሁ አስረጂ ነው። በተለይ የፕሬስ ነፃነት ቀን ሲከበር በአፈፃፀም እዚህም እዚያም የሚታዩ ክፍተቶችን ለመድፈን የሚያስችል ውይይት ማድረግ፣ መነጋገር፣ መከራከር አስፈላጊ ነው። ግን ደግሞ በእዚህ ቀን ብቻ የሚደረግ ዘመቻ ዴሞክራሲውንም ሃሳብን በነፃ የመግለጽ ሕገ መንግሥታዊ መብትንም አያዳብርም። ከመተንፈስ በላይ ያሻንን መፃፍ፣ መናገርም በሚቻልባት አገራችን ስንፈልግ ብቻ አብነቶቻችንን ካልሆኑ ስፍራዎች በመቀላቀል «እለቱን ለማደብዘዝ መሞከር» የነፃ ፕሬስ ነፃ ዘማሪ አያሰኝም።